# የማስረጃ ምዘናና የመሠረታዊ ሕግ ስህተት ልየታ:- የፍርድ ትችት

*መሐሪ ረዳኢ (ዶ/ር)*[*]

## መግቢያ

በኢትዮጵያ የህግ ሥርዓት አንድ ለፍርድ ቤት የቀረበ የክርክር ጭብጥ በማስረጃ ምዘና ሥር የሚወድቅ ነው ወይስ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው የሚለው ጥያቄ ቁልፍ የህግ ጥያቄ ነው። በተለይም በሰበር ሰሚ ችሎት ፊት ይህ ጉዳይ ወሳኝ ነው። ምክንያቱም ጉዳዩ የማስረጃ ምዘና ነው ከተባለ በሰበር አይመረመርም፤ መሠረታዊ የህግ ስህተት ጥያቄ ያስነሳል ከተባለ ግን ሰበር ችሎት ጉዳዩን ሊመረምረው እንደሚገባ ህገ መንግስቱ ደንግጓል። ይህ ጭብጥ የወሳኝነቱን ያህል የማስረጃ ምዘናና መሠረታዊ የህግ ስህተት ድንበሩ የት ነው፤ እንዴትስ ይለያል በሚለው ላይ በህግ ሙያ በተሰለፉት አካባቢ የጠራ አቋም አይታይም። በዳኞች አካባቢም ሁኔታው ከዚህ የተለየ አይደለም።

ከዚህ የተነሳም መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበትና በሰበር መመርመርና መታረም የነበረበት ጉዳይ የማስረጃ ምዘና ነው ተብሎ ሲታለፍ፤ በሌላ በኩል ደግሞ የማስረጃ ምዘና ነው በሰበር መመርመር አይገባውም መባል ሲገባው መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው እየተባለ በሰበር ተመርምሮ ሲሻር ይስተዋላል።

ይህ የፍርድ ትችት አንድ የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ውሳኔ[1] ለማሳያነት አቅርቦ በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ የሚያጠነጥን ሲሆን ቀጣይና ተከታታይ ሙያዊ ውይይት ለመጫር ያለመ ነው።

## 1. የጉዳዩ ሥነ-ሥርዓታዊ ጉዞ

ጉዳዩ የአሠሪና ሠራተኛ የግል ሥራ ክርክር ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሥራ ክርክር ችሎት ነበር። ከሳሽ የተከሳሽ ሠራተኛ የነበረ ሲሆን በህገ ወጥ መንገድ የቅጥር ውሌ ስለተቋረጠ ውዝፍ ደመወዜ ተከፍሎኝ ወደ ሥራ እንድመለስ ይወሰንልኝ፤ ወደ ሥራ የማልመለስበት ህጋዊ ምክንያት ካለም በአማራጭ የተለያዩ ክፍያዎች ተከፍለውኝ ልስናበት የሚል አቤቱታ አቀረበ።

---

[*] በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ህግ ትምህርት ቤት) የህግ ተባባሪ ፕሮፌሰር።

[1] ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት፤ ሰበር መዝገብ ቁጥር 177983፤ ጥር 27ቀን 2012 ተወሰነ (ያልታተመ)።

ተከሳሽ መልስ እንዲሰጥበት ታዞ በሰጠው መልስ፤ ስንብቱ የተከናወነው ህግን በተከተለ መንገድ በመሆኑ መዝገቡ ተዘግቶ ልሰናበት የሚል ነበር።

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ያስተናገደው ችሎት ክርክሩን፤ ህጉንና የጽሁፍ ማስረጃውን መርምሮ እንዲሁም ምስክሮችም አዳምጦ በተከሳሽ የተወሰደው እርምጃ ህጋዊ ነው ብሎ የከሳሽን አቤቱታ ውድቅ አደረገ።

ከሳሽ ጉዳዩን በይግባኝ ወደ ፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወሰደው። ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የይግባኝ አቤቱታውን መርምሮ ያስቀርባል የሚል አቋም ስለያዘ የሥር ተከሳሽ ቀርቦ የቃል መልስ እንዲሰጥበት መጥሪያ ተላከለት። መልስ ሰጭም የሥር ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ መጽናት እንዳለበት አስረግጦ ተከራከረ። ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ግን መዝገቡን መርምሮ፤ የሥር ፍርድ ቤትን ውሳኔ ሽሮና ይግባኝ ባይ የስድስት ወር ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎት ወደ ሥራ እንዲመለስ ወሰነለት።

በዚህ ውሳኔ ላይ መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት ብሎ ያመነው ተከሳሽ የሰበር አቤቱታውን ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቀረበ። አቤቱታው ያስቀርባል ወይም አያስቀርብም ብሎ የመረመረው ሦስት ዳኞች የተካተቱበት የሰበር አጣሪ ችሎት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ መጣራት ያለበት መሠረታዊ የህግ ስህተት አለበት ብሎ ስላመነ መጥሪያና የሰበር አቤቱታው ለሰበር መልስ ሰጭ እንዲደርሰውና መልስ እንዲሰጥበት አዘዘ።

የሰበር መልስ ሰጭ (የሥር ከሳሽ) የጽሁፍ መልስ ሰጠ። የሰበር አመልካችም የመልስ መልስ አያያዘ። አምስት ዳኞች የተሰየሙበት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት መዝገቡን መርምሮ ጉዳዩ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሳይሆን የማስረጃ ምዘና ስለሆነና ከሰበር ችሎቱ ሥልጣን ውጪ በመሆኑ ለሰበር መቅረብ የነበረበት አይደለም በሚል የከፍተኛው ፍርድ ቤት ውሳኔን አጸና፤ መዝገቡም በዚሁ ተቋጨ።

ከዚህ በላይ ጉዳዩ የተጓዘበት የችሎቶች እርከን ሥነ-ሥርዓታዊ ሂደት አብራርተናል። ከዚህ በመቀጠል የክርክሩ የፍሬ ጉዳይና የህግ ይዘት እንመረምራለን።

## 2. የክርክሩ ሂደት

እላይ እንደተገለጸው ጉዳዩ የግል ሥራ ክርክር ነው። ከሳሽ የተከሳሽ ሠራተኛ የነበረ ሲሆን ተከሳሹ የአልኮል መጠጥ ፋብሪካ ነው። ከሳሹ በሥራ ቦታ ሠክሮ በመገኘቱ ተከሳሽ (አሠሪ) ድርጊቱን የሠራተኛ ማህበር ተወካይ በተካተተበት የዲስፕሊን ኮሚቴ አጣርቶ፤ የማጣራት ውጤቱም ከሳሽ በሥራ ቦታ ሠክሮ መገኘቱ በሙሉ ድምጽ አረጋገጠ። ቅጣቱን በተመለከተ ግን የሠራተኛ ማህበሩ ተወካይ ሠራተኛው ከሚሰናበት ይልቅ የመጨረሻ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ይድረሰው ብሎ በድምጽ ሲለይ፤ የአብዛኛው የዲስፕሊን ኮሚቴው አባላት ግን በህጉ በተመለከተው መሠረት ያለ ማስጠንቀቂያ የቅጥር ውሉ እንዲቋረጥ ሲል የውሳኔ ሃሳብ አቀረበ። የተከሳሽ ሥራ አስኪያጅም የውሳኔ ሃሳቡን አጸደቀና ለክሱ መነሻ የሆነው ስንብት ተወሰነ።

ከሳሽ የተከሳሽ እርምጃን በመቃወም በሥራ ቦታ ሠክሬ አልተገኘሁም፤ እንዲያውም ከነጭራሹም መጠጥ አልጠጣሁም። ጠጥቼ እንኳ ብገኝ በህብረት ስምምነቱ[2] መሠረት "በሥራ ቦታ መጠጥ ጠጥቶ የተገኘ" በሚል ሥር የመጀመሪያ ደረጃ ጽሁፍ ማስጠንቀቂያና የአምስት ቀናት ደመወዝ ልቀጣ ይገባል እንጂ ከሥራ እንድሰናበት መደረግ አልነበረበትም ብሎ ክስ መሠረተ።

ተከሳሽ ለክሱ በሰጠው መልስ ከሳሽ በሥራ ቦታ ሰክረው ስለመገኘታቸው ጉዳዩን ባጣራው የዲስፕሊን ኮሚቴ የተረጋገጠ ነው። በሥራ ቦታ ሠክሮ መገኘት ደግሞ በህጉም ሆነ በህብረት ስምምነቱ መሠረት የቅጥር ውሉ ያለማስጠንቀቂያ ማቋረጥ የሚያስችል ጥፋት ነው።

በህብረት ስምምነቱ በሥራ ቦታ መጠጥ ስለመጠጣት የተመለከተው በስካር ደረጃ ያልደረሰውን መጠጥ መጠጣትን ለመከልከል ያለመ ነው። እንደሚታወቀው በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ አንቀጽ 27(1) ሥር ያለማስጠንቀቂያ የሥራ ውልን የሚያቋርጡ ጥፋቶች ከዘረዘረ በኋላ፤ ከእነዚህ በተጨማሪ ሌሎች ጥፋቶች በህብረት ስምምነት ሊወሰኑ እንደሚችሉ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ አንቀጽ 27(1 (ተ)) ተመልክቶ ይገኛል። በዚህ መሠረት ነው በሥራ ቦታ መጠጣትን እንደተጨማሪ ጥፋት በህብረት ስምምነቱ እንዲካተት የተደረገው። ምክንያቱም ተከሳሽ የአልኮል መጠጥ አምራች ድርጅት በመሆኑና አንዳንድ ሠራተኞቹ በሥራቸው አጋጣሚ ለመጠጥ ቅርብ ስለሆኑ አጋጣሚውን እንዳይጠቀሙበት ለመከላከል ታስቦ ነው እንጂ ስካርን ህጉ ካስቀመጠለት ቅጣት በታች ለመቅጣት አይደለም።[3]

አልኮል በባህርዩ ሱስ የሚያስይዝና ደጋግሞ ለመጠጣት በመገፋፋት ወደ ስካር የሚያመራ ሲሆን ስካር ደግሞ በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጁ አንቀጽ 13(4) ከሠራተኛው የሚጠበቀውን በብቁ አእምሮ ሥራ ላይ የመገኘትን ግዴታ የሚጻረር ተግባር በመሆኑ በህብረት ስምምነቱ መጠጣት መከልከሉ መሠረቱ ህጋዊ ከመሆኑም በላይ ዓላማውም ዞሮ ዞሮ ስካርን ለመከላከል መሆኑ ግልጽ ነው።

ተከሳሽ የህጉንና የህብረት ስምምነቱን ዓላማዎች በመግለጽና ክርክሩን በማጠናከር መጠጣትና መስከር የተለያዩ ናቸው። የተለያዩ በመሆናቸውም በህብረት ስምምነቱ በተለያየ ቦታ ተቀምጠዋል። ህጋዊ ውጤታቸውም የተለያየ ነው። የከሳሽ ጉዳይ መስከር ስለመሆኑ እስከተረጋገጠ ድረስ በመጠጣት ድንጋጌዎች ሥር የሚስተናገድበት ሁኔታ አይኖርም ያለ ሲሆን ምስክሮችም አስቀርቦ አስመክሯል። በግንባር ቀርበውና በመሐላ ሥር ሆነው ምስክርነት የሰጡት ሰዎች ከሳሽ

---

2 በድርጅቱ ውስጥ በወቅቱ ጸንቶ የነበረው የህብረት ስምምነት በአዋጁ ውስጥ የቅጥር ውልን ያለማስጠንቀቂያ የሚያቋርጡ ጥፋቶች እንደተጠበቁ ሆነው፤ ተጨማሪ ጥፋቶችና ቅጣቶች በአባሪነት አያይዟል። በአባሪ 8 ሠንጠረዥ 32 ሥር *"ማንኛውም ሠራተኛ ወደ ሥራ ቦታ መጠጥ ጠጥቶ መግባት ወይም በሥራ ሰዓት ጠጥቶ መገኘት፤ የመጀመሪያ ጥፋት ሲሆን የመጀመሪያ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ከአምስት ቀናት ደመወዝ ቅጣት ጋር፤ ሁለተኛ ጥፋት ሲሆን የመጨረሻ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ ከአስር ቀናት ደመወዝ ቅጣት ጋር፤ ሦስተኛ ጥፋት ሲሆን ከሥራ ማሰናበት"* የሚል ተደንግጎ ይገኛል።

3 በርግጥ አንዳንድ ወገኖች ህብረት ስምምነቱ ከህጉ ይልቅ ለሠራተኛው የተሻለ ጥበቃ የሰጠው ነው ተብሎ ሊተረጎም አይገባም ወይ? የሚል ጥያቄ ሊያነሱ ይችላሉ። ነገር ግን የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጁ በጥንቃቄ ሲታይ በጥፋትና በጥቅም መካከል ልዩነት ያደርጋል። ጥፋት ሲሆን ከህጉ በላይ ተጨማሪ ጥፋቶች በህብረት ስምምነት መወሰን ይቻላል (አንቀጽ 27(1)(ተ)። በሌላ በኩል ግን በጥቅም ጉዳይ ከሆነ ህብረት ስምምነቱ ከህግ በታች ጥቅም ሊሰጥ አይችልም (አንቀጽ 134(2)። የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም አሁን በተገለጸው መልኩ ትርጉም ሰጥቶበታል *(በሌ ክፍለ ከተማ እና አቶ ማስረሻ ሁሴን፤ ሰበር መዝገብ ቁጥር 49750፤ ቅጽ 9፤ መጋቢት 30 ቀን 2002)።*

በተጠቀሰው እለት "አፉ ጋን ጋን ይሸት እንደነበር"፣ "ምላሱ ተሳስሮ ይንተባተብ እንደነበር"፣ ይህንን የተገነዘቡ የቅርብ አለቃው "አንተ ሰክረሃል እንዴ?" ሲሉት፣ "አዎን! ምን አገባህ?" ብሎ እንደጮሀባቸው መስክረዋል።

ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ያስተናገደው የሥራ ክርክር ችሎትም ፍሬነገሩን፣ ህጉንና ማስረጃዎቹን አገናዝቦ "በተከሳሽ የቀረቡት ምስክሮች ከሳሽ በሥራ ቦታ ስክረው እንደነበረ፣ በኃላፊያቸው ላይ ኃይለ ቃል የተናገሩ መሆናቸው ስለተረጋገጠ ተከሳሽ የወሰደው እርምጃ ህጋዊ ነው" ሲል ወሰነ። ነገር ግን ከላይ እንደተገለጸው ከሳሽ ይግባኝ በማቅረቡ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ክርክሩን ከሰማ በኋላ ስካር ምንድን ነው? የሚል ጭብጥ ይዞ በሚከተለው መንገድ እልባት ሰጠው።

ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ስካር ምን እንደሆነ በህግ ትርጉም እንዳልተሰጠው በማስገንዘብ ነገር ግን "በተለምዶ የሰከረ ሰው ይንገዳገዳል፣ ይወድቃል፣ ይጮሃል፣ አካባቢን ይረብሻል" ካለ በኋላ በተያዘው ጉዳይ ግን ይግባኝ ባይ እነዚህን ባህሪያት ስለማሳየቱ አልተመሰከረም። የተመሰከረው አፉ አልኮል ይሸት ነበር፣ ይንተባተብ ነበር የሚል ነው። ይህ ደግሞ "ሞቅታ" ከሚባል በስተቀር ስካር ሊባል የሚቻል አይደለም፣ በመሆኑም ይግባኝ ባይ "በሥራ ቦታ መጠጣት" በሚል ሥር ህብረት ስምምነቱ ያስቀመጠው የመጀመሪያ ደረጃ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያና የአምስት ቀናት ደመወዝ መቀጣት ሲገባው እንዲሰናበት መወሰኑ ተገቢ አልነበረም። ስለዚህ ይግባኝ ባይ ከስድስት ወር ውዝፍ ደመወዝ ጋር ወደ ሥራ ይመለስ፣ የመጀመሪያ ደረጃ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያና የአምስት ቀናት ደመወዝ ቅጣት ይድረሰው ብሎ የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔን ሽሯል።

እንደሚታወቀው በመደበኛው የፍትሐ ብሄር ሥነ-ሥርዓት ህግ መሠረት የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ከተሻረ ሁለተኛ ይግባኝ የሚፈቀድ ቢሆንም በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ከጸና ግን የመጨረሻ ነው። በአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ አዋጅ መሠረት ግን ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሥር ፍርድ ቤት ውሳኔን ቢያጸናም ሆነ ቢሽር፣ ይግባኝ የማይባልበትና የመጨረሻ ነው።[4] ስለሆነም በዚህ ጉዳይ ሌላ የይግባኝ እድል ስለሌለ ያለው ብቸኛ አማራጭ የሰበር አቤቱታ ማቅረብ ነው።

የሰበር አቤቱታ አቅርቦ ተቀባይነት ለማግኘት ግን በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር ተሰኝቻለሁ ማለት ብቻ በቂ አይደለም። ከዚህ በተጨማሪ የይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆኑን ማስረዳት የግድ ይላል። በዚህም መሠረት የሰበር አመልካች የሰበር አቤቱታውን ሲያቀርብ 'የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በተያዘው ጉዳይ ላይ ውሳኔ ሲሰጥ መሠረታዊ የህግ ስህተት ፈጽሟል፣ ምክንያቱም ስካርን ሲተነትን የቀረጸው ትርጓሜ መሠረታዊ ችግር ያለበት ነው፣ አንድ ሰው ጠጥቶ ካልተንገዳገደ፣ ካልወደቀ፣ ካልጮኸና አካባቢውን ካልረበሸ ሰከረ አይባልም የሚለው የፍርድ ቤቱ ትንተና መሠረታዊ የሕግ ስህተት የሚንጸባረቅበት ነው' ብሎ መከራከር አለበት።

በርግጥ ፍርድ ቤቱ ስካርን የገለፀበት መንገድ በጎዳና ለሚንቀሳቀስ ሰው ሊያገለግል ይችል ይሆናል። ነገር ግን ከሳሽና ተከሳሽ በአውራ ጎዳና የተገናኙ አይደሉም። በውል ታስረው፣ መብትና

[4] የአሠሪና ሠራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 140(2)።

ግዴታ አቋቁመው ግንኙነት የፈጠሩ ናቸው። ከሳሽ ለሥራ ብቁ በሆነ የአካልና የአእምሮ ሁኔታ በሥራ ላይ በመገኘት፤ ሙሉ እውቀቱንና ጊዜውን ተጠቅሞ ለተከሳሽ አገልግሎት ሊያበረክት፤ ተከሳሽ ደግሞ ለተበረከተለት አገልግሎት ደመወዝ ሊከፍል የገቡበት ግዴታ በአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት ዘርፍ ስካር ሲተረጎም ለዚህ በውል ለተቋቋመ ግብ ከሚኖረው እንድምታ አንጻር መሆን ይኖርበታል። የከፍተኛው ፍርድ ቤት ግን በዚህ መነጽር አልቃኘውምና መሠረታዊ የህግ ስህተት ፈጽሟል የሚል ይዘት ያለው የሰበር አቤቱታ ለፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርቧል።

አቤቱታው በሰበር አቤቱታ አጣሪው ችሎት ተመርምሮ "ከፍተኛው ፍርድ ቤት ጉዳዩን ሲመረምር በሥር ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪ መጠጥ ጠጥቶ ሥራ ላይ መገኘቱ፤ እየተንተባተበ እንደነበር መመስከሩ ቢገለጽም ከዚህ ውጪ የሆኑት የስካር ምልክቶች ማለትም ወድቆ መገኘትን፤ መንገዳገድንና መጮህን ባለማሳየቱ በህብረት ስምምነቱ ሠንጠረዥ የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ እና የአምስት ቀን ደመወዝ የሚያስቀጣ እንጂ ሊሰናበት አይገባም ሲል የሰጠው ውሳኔ መጣራት ያለበት መሆኑ ስለታመነበት ጉዳዩ ለሰበር ችሎት ይቅረብ፤ መልስ ሰጪ መልስ ይስጥበት ብለናል" የሚል ብይን ተሰጥቶበታል።

የሰበር መልስ ሰጭ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያስተላለፈው ውሳኔ መሠረታዊ የህግ ስህተት ስለሌለበት ሊጸና ይገባል፤ ስካር አለ ለማለት መለካት ያለበት በውጤቱ ነው። ከስካሩ በመነጨ በሌላ ሰው ላይ ጉዳት ስለመድረሱ ማስረጃ ባልቀረበበት ሁኔታ ስካር አለ ሊባል አይገባም የሚል ከህጉ ዓላማና ግብ ጋር የማይገናኝ ክርክር አቅርቧል።

ምንም እንኳ ሦስት ዳኞች የተሰየሙበት የሰበር አጣሪ ችሎት ጉዳዩ መሠረታዊ የህግ ክርክር የሚያስነሳ መሆኑን አምኖ ያስቀርባል ብሎ ብይን ቢሰጥም፤ ጉዳዩን በመጨረሻ የመረመረው አምስት ዳኞች የተሰየሙበት ሰበር ሰሚ ችሎት ግን "የሰበር አቤቱታው የቀረበው ድርጊቱ ስካርን ያሳያል በሚል ሲሆን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በህገ መንግስቱ አንቀጽ 80(3) ሆነ በየፌዴራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር 25/1988 አንቀጽ 10 ላይ በመጨረሻ ውሳኔ ላይ በተፈጸመ መሰረታዊ የህግ ስህተት እንጂ ማስረጃው ተመዝኖ የተደረሰበትን የፍሬ ነገር ድምዳሜ ላይ እንዲመለከት ሥልጣን አልተሰጠውም" በማለት የጉዳዩን ጭብጥ ወደ ማስረጃ ምዘና ቀይሮ "እኔን የሚመለከት አይደለም፤ ማስረጃውን የተቀበለው ፍርድ ቤት ማስረጃውን መዝኖ ስካርን አያመለክትም የሚል አቋም ከያዘ በሰበር የሚመረምርበት ህጋዊ መሠረት የለም" በማለት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔን በማጽናት ፋይሉን ዘግቶታል።

## 3. ትችት

ለመሆኑ ይህ መዝገብ ያስነሳው ጭብጥ የማስረጃ ጉዳይ ነው ወይስ መሠረታዊ የህግ ስህተት? የሚል ጥያቄ በጥሞና መመርመር ይገባል። በዚህ ረገድ የሰበር አጣሪው ሦስቱም ዳኞች ጉዳዩ መሠረታዊ የህግ ስህተት ነው ብለው ስላመኑ በሙሉ ድምጽ ያስቀርባል ብለው ለተጨማሪ ምርመራ ወደ መደበኛው ሰበር ሰሚ ችሎት መርተውታል። በሌላ በኩል ደግሞ የሰበር ሰሚ

ችሎቱ አምስት ዳኞች ጉዳዩ የማስረጃ ምዘና ነው ብለው ስላመኑ የሰበር አቤቱታውን በሙሉ ድምጽ ውድቅ አድርገውታል።

እንግዲህ የማስረጃ ምዘና ሲባል ውሳኔ ሰጪው አካል ለጉዳዩ የቀረቡትን ማስረጃዎች ተገቢነታቸውን፣ ተቀባይነታቸውንና ክብደታቸውን መዝኖና የሚገባቸውን ዋጋ ሰጥቶ ለውሳኔው መሰረት የሚያደርግበት አግባብ ነው። ከዚህ አንጻር በተያዘው ጉዳይ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የፈጸመው ተግባር የማስረጃ ምዘና ብቻ ነው ወይ?

በዚህ ፀሃፊ ግንዛቤ የከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ጉዳዩን ለመፍታት ሁለት እርምጃዎችን ወስዷል። አንደኛ ለስካር ትርጉም ሰጥቷል። ምክንያቱም ፍርድ ቤቱ ስካር ምን እንደሆነ የህግ ትርጉም እንዳልተሰጠው በማስገንዘብ በተለምዶ ግን የሰከረ ሰው ይንገዳገዳል፣ ይወድቃል፣ ይጮሃል፣ አካባቢን ይረብሻል የሚል የራሱ ትርጉም ሰጥቷል። ሁለተኛ ራሱ ምስክሮችን ባይሰማም በሥር ፍርድ ቤት የተደመጡት ምስክሮች የሰጡት የምስክርነት ቃል ከመዝገቡ አይቶ ለስካር ከሰጠው ትርጉም አንጻር መዝኗል። ስለዚህ የከፍተኛው ፍርድ ቤት በተያዘው ጉዳይ ያከናወነው ተግባር የማስረጃ ምዘና ብቻ ነው ሊባል የሚቻል አይደለም።

የሰበር አጣሪው ችሎት የከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ለስካር የሰጠው ትርጉም አግባብነትና ህጋዊነት መመርመር ይገባዋል ብሎ ስላመነ ያስቀርባል ብሎ ወሰነ። መደበኛው የሰበር ችሎት በበኩሉ የመጀመሪያው ከፍተኛው ፍርድ ቤት ተግባር ግምት ውስጥ ሳያስገባ ትኩረቱን በሁለተኛው ተግባር ላይ በማሳረፍ ከፍተኛው ፍርድ ቤት ያከናወነው የማስረጃ ምዘና ነው የሚል አቋም አራመደ። እንግዲህ ቁልፉ ልዩነትና ችግር እዚህ ላይ ነው። የሰበር አጣሪው ችሎት "ነገርን ከስሩ፣ ውሃን ከጥሩ" እንዲሉ ጉዳዩን ከሥረ መሰረቱ ጀምሮ ይዞት ነበር።

መደበኛው የሰበር ችሎት ግን ጉዳዩን ከሥሩ የመረመረው አይመስልም። ሰበር ሰሚ ችሎቱ በውሳኔው መንደርደሪያ "የሰበር አቤቱታው የቀረበው ድርጊቱ ስካርን ያሳያል በሚል ነው" ብሎ መነሳቱ የሰበር አቤቱታውን ይዘት በአግባቡ አለመገንዘቡን ያሳያል። ምክንያቱም የሰበር አቤቱታው ከፍተኛው ፍርድ ቤት ለስካር የሰጠው የህግ ትርጉም መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበትና መታረም ይገባዋል በሚል እንጂ ድርጊቱ ስካርን ያሳያልና ስካር ነው ይባልልን የሚል የማስረጃ ምዘና ጉዳይ አልነበረም። በተጨማሪም የከፍተኛው ፍርድ ቤት ማስረጃ ከመመዘኑ በፊት ለስካር የራሱ ትርጉም መስጠቱ እየታወቀ የዚህ ትርጉም ተገቢነትና ህጋዊነት መመርመር ሲገባው ሰበር ችሎቱ ትኩረት አልሰጠውም።

የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስካርን በጠባቡ በመተርጎም "ሰው ካልተንገዳገደ፣ ካልወደቀና ጮሆ አካባቢውን ካልረበሸ ሰከረ አይባልም" ብሏል። ይህ በትርጉምነት የተጠቀመበት መንደርደሪያ ተገቢ ነው ወይ? በተለይም ጉዳዩ ከተነሳበት ከአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት እንዲሁም ሠራተኛው ከሚሠራበት የአልኮል መጠጥ ፋብሪካና የህብረት ስምምነቱ ዓላማ አንጻር ከፍተኛው ፍርድ ቤት ስካርን የተረጎመበት መንገድ ምን ያህል ያስኬዳል ብሎ መመርመር ይገባ ነበር።

እንደሚታወቀው በአሠሪና ሠራተኛ ህጉ አንቀጽ 14(2) መሠረት ሠራተኛ በሥራ ቦታ ሠክሮ መገኘት ህገ ወጥ ድርጊት ነው። ይህ ክልከላ የተቀመጠው ሠራተኛው ተንገዳግዶ እንዳይወድቅና

እንዳይጎዳ ለመጠበቅ፤ እንዲሁም ጮሆ አካባቢን እንዳይረብሽ ጸጥታ ለማስከበር ብቻ ነው ወይ? ሌላ ተጨማሪ ዓላማና ግብ የለውም ወይ? ብሎ መመርመር ይገባ ነበር።

እላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው የአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት ሠራተኛው አገልግሎት እንዲያበረክት፤ አሠሪው ደግሞ ለተበረከተለት አገልግሎት ደመወዝ መክፈል የሚገደድበት ስርዓት ነው። ሠራተኛው አገልግሎቱን የሚያበረክተውም በአሠሪው መሪነት ነው። የአሠሪው መሪነት ለማስፈጸም ያሙች ዘንድ ደግሞ ሠራተኛው በአዋጁ አንቀጽ 13 መሰረት ብቁ በሆነ የአካልና የአእምሮ ሁኔታ በሥራ ቦታ የመገኘት ግዴታ በህግ ተጥሎበታል። ስካር ደግሞ መንገዳገድና መውደቅ ባያስከትልም ብቁ በሆነ የአካልና የአእምሮ ሁኔታ የመገኘት እድልን ያጓድላል።

በርግጥ በጎዳና ለሚንቀሳቀስ መንገደኛ ሰከረ ለማለት መንገዳገድ፤ መውደቅና ጮሆ አካባቢን መረበሽ መለያ ምልክቶች ሊሆኑ ይችላሉ። የጎዳናው የስካር ትርጉም ግን በአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት ለተሳሰሩ ወገኖች የሚያገለግል አይሆንም። ምክንያቱም አሠሪና ሠራተኛ ግንኙነታቸው የጎዳናና የእግረ መንገድ ሳይሆን የውል ነው። ስካር የሚለው ቃል በአሠሪና ሠራተኛ ህጉ ውስጥ ሲካተትና ሲከለከል የተለምዶ ቋንቋ ሳይሆን የህግ ቋንቋ ሆኗል ማለት ነው። በመሆኑም ህግ ትርጉም ያልሰጠባቸው የህግ ቃላትና ሀረጎች ሲያጋጥሙና ህግ ተርጓሚው አካል ትርጉም እንዲሰጣቸው አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከዓላማቸው አንጻር ሊመለከታቸው ይገባል። ከዚህ አኳያ ሲታይ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ ትንተና ግድፈት አለበት።

እላይ እንደተገለጸው የሰበር አጣሪው ችሎት ክርክሩን በአግባቡ ተገንዝቦ ያስቀርባል ብሎ ወሰነ። በአንጻሩ መደበኛው ሰበር ችሎት ጉዳዩን መርምሮ የማስረጃ ምዘና ነው፤ የማስረጃ ምዘና ጉዳይ ደግሞ ምስክሮቹን ላዳመጠ ፍርድ ቤት መተው ያለበት እንጂ መሠረታዊ የህግ ስህተት ተብሎ በሰበር የሚመረመርበት የህግ መሰረት የለም ብሎ በሙሉ ድምጽ ወሰነ። መደበኛ ሰበር ችሎቱ ያልተገነዘበው ጉዳይ ግን የከፍተኛው ፍርድ ቤትም ቢሆን ምስክሮች አስቀርቦ አላዳመጠም። ምስክሮች ቀርበው የተደመጡት በዲስፐሊን ኮሚቴ ፊትና በመጀመሪያው ደረጃ ፍርድ ቤት ፊት ብቻ ነው። እነዚህ ሁለት መድረኮች ደግሞ እላይ እንደተገለጸው ሁኔታው ስካር እንደነበር አረጋግጠው መዝግበዋል። ስለዚህ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ያላዳመጠውን የምስክሮች ቃል በሥር ፍርድ ቤት መዝገብ ተመስርቶ ነው የመዘነው።

ለነገሩ የሥር ፍርድ ቤት ከመዘገበው የምስክሮቹ ቃልም ቢሆን ከፍተኛው ፍርድ ቤት ለራሱ የሚጠቅመውን ብቻ መርጦ ነው ለውሳኔው መሠረት ያደረገው። ለምሳሌ በመዝገቡ የሠፈረው የምስክሮች ቃል "ከሳሽ አፉ ጋን ጋን ይሸት ነበር፤ ይተባተብ ነበር፤ የቅርብ አለቃው ሰክረሃል እንዴ ብሎ ሲጠይቀው አዎን ሰክሬአለሁ ምን አገባህ ብሎ ጮሆበታል" ይላል። ከፍተኛው ፍርድ ግን ከሳሽ አለቃው ላይ ጮሆበታል የሚለው የምስክርነት ቃል ለስካር ለሰጠው ትርጉምና ለመደምደሚያው የሚመች ሆኖ ስላላገኘው ከፍርድ ትንተናው ውስጥ አላካተተውም። ከተመዘገበው የምስክርነት ቃል ለራሱ የሚጠቅመውን ብቻ ለይቶ መውሰድም ተገቢ የዳኝነት አሠራር አይደለም። እንግዲህ እንዲህ ያለ ክፍተት ያለውን የማስረጃ ምዘና ነው ሰበር ሰሚው ችሎት እንዲጸና እድል የሰጠው።

## ማጠቃለያ

የሰበር ሰሚ ችሎቱ የተዛነፈውን የከፍተኛ ፍርድ ቤት ውሳኔ እንዳለ ከማጽደቅ ይልቅ ፍርድ ቤቱ ለስካር የሰጠውን ትርጉም መርምሮ ለወደፊቱ ቢያንስ ለአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነት የሚመጥን የስካር ትርጉም ሰጥቶ ከሳሹ አልሰከረምና ከሥራ ሊሰናበት አይገባም ብሎ ውሳኔውን ማጽናት በቻለ ነበር። በዚህ ፀሃፊ እምነት የሰበር ሰሚ ችሎቱ ችግር የከፍተኛውን ፍርድ ቤት የተዛባውን የስካር ትርጉም እንዳለ መቀበሉና ማለፉ እንጂ የበታች ፍርድ ቤቱን ፍርድ ማጽደቁ አይደለም።

ይህ እንዳለ ሆኖ ከዚህ በላይ ለማሳየት እንደሞከርነው አንድ ጉዳይ የሚያስነሳው ጭብጥ የማስረጃ ምዘና ነው ወይስ የመሠረታዊ የህግ ስህተት የሚለውን ለመወሰን ነገሩን ከሥረ መሰረቱ ካልተመረመረ በቀር መለየት አስቸጋሪ ነው። አሁን ባለን የህግ ሥርዓት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የመጨረሻው የፍትህ ምንጭ ነው። የመጨረሻነቱን ያህል ባለጉዳዮችም የመጨረሻ እድላቸው በመሆኑ ከሰበር ችሎቱ ብዙ ይጠብቃሉ። ጠበቅ ያለ ጉዳዩን ከሥረ መሠረቱ አንስቶ ምርመራ የሚያከናውን ሰፊ ትእግስት ያለው፣ በሰል ያለ የህግ ትንተናና ከህጉ ቃላት ይልቅ የህጉን መንፈስ የሚረዳና ጥልቅ ማህበረሰባዊ ግንዛቤ ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ይጠበቃል። አልፎ አልፎ ግን የተጠበቀውን ያህል እያገኘን ነው ወይ የሚለው የሚያወያይ ነው።

ሌላው በሰበሩ አሠራር የተገነዘብነው ጉዳይ የሰበር አቤቱታ የሚጣራው ሦስት ዳኞች በያዘ ችሎት ሲሆን፣ ያስቀርባል ተብሎ ከተወሰነ በኋላ ደግሞ ጉዳዩ የሚመረመረው ካጣሩት ውጪ በሆኑ አምስት ዳኞች ነው። አጣሪው ችሎት የሰበር አቤቱታውን አጥንቶና መርምሮ ነው ለሰበር ያስቀርባል ወይም አያስቀርብም ብሎ የሚወስነው። ይህ ሁሉ ሲያደርግ አጣሪው ችሎት ጉዳዩን ከሌላው በተሻለ በቅርበትና በጥልቀት የመመርመር እድል አለው ተብሎ ይታመናል። በዚህ ሂደት ጉዳዩን በቅርበት የተረዳው ሦስት አባላት ያሉት አጣሪ ችሎት ሌሎች ሁለት ዳኞች ተጨምረውለት ለጉዳዩ እልባት እንዲሰጥ ማድረግ ሲገባ፣ ወደ ሌሎች አምስት ዳኞች ተመርቶ እንዲወሰን ማድረግ ነገሩን "አድሮ ቃሪያ" እንዲሆን ሊያደርገው ይችላል።

በእርግጥ አልፎ አልፎ የሚደመጠው አጣሪው ችሎት አንድ መድረክ፣ መርምሮ ውሳኔ የሚያሳርፍ ደግሞ ሌላ አድርጎ መመደብ ለሥልጣን ገደብና ቁጥጥር (check and balance) ጠቀሜታ አለው የሚል ነው። ለነገሩ የሥልጣን ገደብና ቁጥጥር ጽንሰ ሃሳብ የመጣው በሦስቱ መንግስታዊ አካላት ማለትም በህግ አውጪው፣ በአስፈጻሚውና በዳኝነት አካሉ መካከል የሚኖረው መስተጋብር ለመለየት የተደራጀ አሰራር ነው። በመሆኑም ይህንኑ ለተለየ ዓላማ የተደራጀ ጽንሰ ሃሳብ በዳኝነት የውስጥ አሠራር እንዲሠራበት የማድረጉ ተገቢነት አጠያያቂ ነው። የዳኝነት አካሉ ለአፈጣጠሩ የሚያመች የራሱ የሥልጣን ገደብና ቁጥጥር ሥርዓት እንዳለው ሊታመን ይገባል። ለሥልጣን ገደብና ቁጥጥር ተብሎ አንዱ ዳኛ ምስክር ያዳምጥ፣ ሌላ ዳኛ ደግሞ በመዝገቡ ላይ ውሳኔ ይስጥ ቢባል ምስክር ያላዳመጠ ዳኛ "ነገር በዓይን ይገባልና" ምን ያህል ለመወሰን እንደሚቸገር መገንዘብ አያዳግትም። የአሁኑ የሰበሩ አሠራር ከዚህ ጋር የሚመሳሰል ነው፣ መርማሪ አጣሪው ችሎት ሆኖ ውሳኔ የሚሰጠው ደግሞ መደበኛው ሰበር ችሎት ነው።

ከዚህም በተጨማሪ እንዲህ ዓይነት አሠራር ሰበር ችሎቱ ካለው የፋይል ብዛትና የሥራ ጫናም ጋር የሚጣጣም አይደለም። ለአንድ የሰበር መዝገብ መጀመሪያ በሦስት የአጣሪ ችሎት ዳኞች ያስቀርባል ወይም አያስቀርብም ተመርምሮ፤ ያስቀርባል ከተባለ ደግሞ በሌሎች አምስት ዳኞች በአጠቃላይ በስምንት ዳኞች የሚስተናገድ ይሆናል ማለት ነው። ሰበሩ ባለው የሥራ ብዛትና የፋይል ጫና እንዲህ ብሎ የሚዘለቅና የሚያዛልቅ አይመስልም።

* * *